ኮሚኒኬ ቁጥር 7 ህዳር 9 ቀን 2010 ዓ.ም.

# የኢ.መ.ድ.ሠራተኞች ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ላይ ተሳተፉ

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ለ 18ኛ ጊዜ **"ሴቶችን እናብቃ የነገ መሪዎች ናቸው"** በሚል መሪ ቃል ባዘጋጀው ውድድር የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ሠራተኞችን ጨምሮ ሌሎች ከ500 በላይ የውጪ ሀገር ተሳታፊዎችን ያካተተ በጠቅላላው አርባ አራት ሺህ ያህል ተወዳዳሪዎች የተሳተፉበት ውድድር ኅዳር 9 ቀን 2011 ዓ.ም. ተከናወነ፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ላይ ሠራተኞቹን በየዓመቱ የሚያሳትፍ ሲሆን ይህም ጤናቸውን ለመጠበቅ የራሱን ሚና እንደሚጫወት ይታወቃል፡፡ የዘንድሮ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በአዲስ አበባ የሚገኙ ከዋናው መስሪያ ቤት፣ ከሪከቨሪ፣ ዲስትሪክቶችና ቅርንጫፎች የተውጣጡ ሁለት መቶ ሃምሳ ሠራተኞች በውድድሩ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ለ18ኛ ጊዜ የተካሄደ ሲሆን የውድድር ቦታውን በአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ ምክንያት ከመስቀል አደባባይ ወደ ስድስት ኪሎ የቀየረ ሲሆን መነሻውን በስድስት ኪሎ አድርጎ በቀበና ሾላ አድርጎ በባምቢስ በመታጠፍ & በአድዋ ድልድይ፣ በአራት ኪሎ አድርጎ ስድስት ኪሎ የተጠናቀቀ ሲሆን ባጠቃላይ ውድድሩ አስር ኪሎ ሜትር የሸፈነ መሆኑ ታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ሠራተኞቹን የመሮጫ ቲሸርትና በሩጫው ላይ ጉዳት ቢገጥማቸው እንዳይቸገሩ የመድን ሽፋን በመግዛት እንዲሮጡ ሲያደርግ ከጤንነት ጎን ለጎን ዓላማውን አድርጎ የሚሰራው በሩጫው ላይ የሚሳተፉ ሠራተኞች የድርጅቱ አርማ ያለበትን ቲሸርት በመልበስና በጋራ በመሆን የጋራ ፎቶ ተነስተው እንዲሮጡ በማሰብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዋናው መስሪያ ቤት እየተገኙ የታሰበውን የሚፈጽሙ በጣም ጥቂቶች ስለሆኑ ለወደፊቱ የተመዘገቡ በሙሉ በጋራ መሮጥ እንዲችሉ ድርጅቱ ያሳስባል፡፡




**ከኢ.መ.ድ. ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ላይ የተሳተፉ ሠራተኞች በከፊል**

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና ተወዳጅ እየሆነ የመጣ ዝግጅት ሲሆን ከፍተኛ ተወዳዳሪዎችን በማሳተፍ ከአፍሪካ ቀዳሚ ውድድር መሆኑ ይታወቃል፡፡